## ራያ ዩኒቨርሲቲ የተለያዩ እቃዎች በግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል

- የተለቀቀበት ቀን: ረቡዕ ጳጉሜን 4, 2012 (ከ 5 ዓመታት)
- መዝግያ ቀን: መስከረም 14, 2013 4:00 ጥዋት (ተዘጋ)
- የጨረታ ማስከበርያ ዋጋ:በየሎቱ የተለያየ ነዉ
- ቦታ:ማይጨዉ
- የጨረታ ደኩመንት ዋጋ:200
- ጨረታ ሚከፈትበት ቀንና ሰዓት: መስከረም 14, 2013 4:30 ጥዋት
- ምድብ: ናይ ንፅህናን ፅሬት ኣቁሑት/ ኮምፒተርን ተዛመድቲ / ናይ ኮምፒተር ተዛመድቲ አቁሑትን/ ኮንስትራክሽን ማሽነሪን ኣቁሑትን/ ኮንስትራክሽን ጥረ ኣቁሑት/ ኤሌክትሪካልን መሳርሕታትን መለዋወጢን/ ኤሌክትሮ-መካኒክስ ኣቁሑትን ግልጋሎትን/ መለዋወጢ ኣቁሑት መኪና/ ናይ ምህንድስና ኣቁሑት/ ኣቅርቦት ምግቢ / መኪና ክራይ/ ጨርቃ መርቂን ኣልባሳትን/

ጨረታዉ በኣዲስ ዘመን ጋዜጣ የወጣበት ቀን: 4/13/2012

ጨረታዉ የሚዘጋበት ቀን:  በ16ኛዉ ቀን ከጠዋቱ 4:00 ሰዓት

ጨረታዉ የሚከፈትበት ቀን: በ16ኛዉ ቀን ከጠዋቱ 4:30 ሰዓት

ጨረታ ቁጥር ራዩ/ግአዳ/001/2013 በጀት ዓመት

| ምድብ | የእቃ/አገልግሎት ዓይነት | የጨረታ ማስከበርያ ዋስትና መጠን ብር | የጨረታ ማስከበርያ ዋስትና | የጨረታው የሚዘጋበት ቀን | ጨረታው የሚከፈትበት ቀንና ሰዓት |
|---|---|---|---|---|---|

ምልክታ እና ቅጂው:: 2013 - 2026 Made with love in Mekelle

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ምድብ 1 | የደንብ ልብስ ግዥ | 20,000.00 | ከታወቀ ባንክ | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 2 | የእንጀራ አቅርቦት | 20,000.00 | የሚሰጥ የክፍያ | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 3 | የፅዳት ዕቃዎች | 200,000.00 | ማዘዣ ቼክ | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 4 | ለአይሲቲ የሚያገለግሉ እቃዎች | 120,000.00 | /cpo/ወይም ‹ በሁኔታዎች ላይ | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 5 | ለመካኒካል ኢንጅነሪንግ ት/ክፍል የሚውሉ እቃዎች | 75,000.00 | ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 6 | የአርማታ ብረት | 122,000.00 | ( በባንክ የተረጋገጠ | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 7 | የአውቶሞቲቭ ላቦራቶሪ እቃዎች | 120,000.00 | ሌተር ኦፍ ክሬዲት | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 8 | የኤሌክትሪካልና ኮምፒዩተር እንጂነሪንግ ላቦራቶሪ እቃዎች | 75,000.00 | | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 9 | የማኑፋክቸሪንግ እንጂነሪንግ እቃዎች | 120,000.00 | | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |
| ምድብ 10 | የመኪና ኪራይ | 10,000.00 | | 4:00 | 16ኛው ቀን | 16ኛው ቀን 4:30 |

ራያ ዩኒቨርሲቲ ከላይ በሰንጠረዡ በምድብ የተዘረዘሩትን በብሄራዊ ግልፅ ጨረታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል:: ስለሆነም በጨረታው መወዳደር የምትፈልጉ ተጫራቾች ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው።

1. ተጫራቾች የ2012/2013 ዓ.ም የታደሰ ለየምድቡ በዘርፉ ህጋዊ የንግድ ስራ ፈቃድ፤ የዘመኑን ግብር መክፈላቸውን የሚረጋግጥ ከግብር ሰብሳቢ ባለሥልጣን ጊዜው ያላለፈበት ምስክር ወረቀት ወይም ታክስ ክሊራንስ፣ የግብር ከፋይነት ምዝገባ ሰርተፊኬት፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት እና የፌዴራል የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ባዘጋጀው የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ መካተታቸውን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለባቸው።
2. ከምድብ 1 እስከ ምድብ 10 ላሉት ምድቦች ለእያንዳንዳቸው የጨረታ ሰነድ መሸጫ የማይመለስ ብር 200.00 (ሁለት መቶ ብር) ብቻ በመክፈል ጨረታው በጋዜጣ ከወጣበት ወይም አየር ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ ለተከታታይ 15 ቀናት በራያ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 5 ግዥ ቡድን 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 207 በመምጣት መውሰድ ይቻላል ።
3. ተጫራቾች ከምድብ 4 በስተቀር ፋይናንሽያል ሰነዳቸው አንድ ኦርጂናልና አንድ ኮፒ ከነሙሉ ህጋዊ መስፈርቶች ያሟላ፣ ለምድብ 4 ደግሞ በሁለት ኤንቬሎፕ ሁኖ ቴክኒካል ኦርጂናልና ፋይናንሽያል ኦርጂናልን እንዲሁም ቴክኒካል ኮፒ እና ፋይናንሽያል ኮፒ ከነ ሙሉ ህጋዊ መስፈርቶች በተለያየ ፖስታ በማሸግና በደማቅ ቀለም ተፅፎ የጨረታ ሳጥኑ ከመዝጋቱ በፊት ጨረታው አየር ላይ ከዋለበት በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ በ4:00 ሰዓት በግዥ አስተዳደር ዳይሬክቶሬት አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 5 ግዥ ቡድን 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 207 ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይችላሉ።
4. ጨረታው በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ በ4:30 ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በዩኒቨርሲቲው ዋናው ግቢ ውስጥ በግዥ አስታዳደር ዳይሮክቶሬት አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 5 ግዥ ቡድን 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 207 ይከፈታል።

- 5. ጨረታው ፀንቶ የሚቆየው ጨረታው ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ለምድብ 4፣ 5፣ 6፣ 7፣ 8 ና 9 120 (አንድ መቶ ሃያ ቀናት) ለምድብ 1፣ 2፣ 3 ና 10 ደግሞ 90 (ዘጠና) ቀናት ይሆናል።
- 6. በምድብ 1 እና ምድብ 4 የዋጋ ግምገማ በምድ (ሎት ዋይዝ) ነው።
- 7. የጨረታ ማስከበርያ ከታወቀ ባንክ በሚሰጥ የክፍያ ማዘዣ ቼክ ወይም በሁኔታዎች ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ወይም በባንክ የተረጋገጠ ሌተር ኦፍ ክሬዲት ለምድብ 4 ጨረታ በቴክኒካል ኦርጂናል ሰነዶች ማሸጊያ ፖስታ እንዲሁም ለሌሎቹ 9 ምድቦች ደግሞ በፋይናንሻል ኦርጂናል ሰነዶች ማሸጊያ ፖስታ ታሽጎ መቅረብ ይኖርበታል።
- 8. አሸናፊ የሆኑ ተጫራቶች እቃዎችን በራሳቸው ትራንስፖርት ራያ ዩኒቨርሲቲ ዋናው ግቢ ድረስ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።
- 9. ዩኒቨርሲቲው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

ለበለጠ መረጃ፡- WWW.rayu.org ወይም

በስልክ ቁጥር 0348770501/0342478375/0348770546

ራያ ዩኒቨርሲቲ